# ፖለቲካ በኢትዮጵያ

አስራት አብርሃም

የዚህ ፅሁፍ ዓላማ “ፖለቲካችን ውጤት የራቀው ለምንድነው? ውጤታማ እንዲሆንስ ምን መደረግ አለበት?” ለሚለው ጥያቄ የራሴ ሀሳብ ለማስቀመጥ ነው። ከአሁን በፊትም **“ፖለቲካዊ ትግሉ እስትራቴጂካዊ ለውጥ ያስፈልገዋል”** የሚል ርዕስ በኢትዮ-ሚዲያ ድሕረ ገፅ እንዲነበብ አድርጋለሁ። ይህን መልዕክት በስፋትና በተሻለ መንገድ ወደ ህዝቡ እንዲደርስ በማሰብም “መለስና ግብፅ” በሚለው የመጣጥፍ ስብስብ ውስጥ እንዲካተት ተደርጎ ታትሟል። በዚሁ መፅሐፍ ውስጥ ከተካተቱት ወጎች ለየት ያለ ይዘት ያለው ፅሁፍ ነው። ሆኖም ያ በራሱ በቂ መስሎ ስላልታየኝ ነው አሁንም ተጨማሪ ነገር ለማለት የፈለኩት።

ስለአገራችን ፖለቲካ ስንናገር በመጀመሪያ ስለባለድርሻዎቹ ማንሳት ተገቢ ነው። ፖለቲካው የሰፊው ህዝብ ተሳትፎ ያልነበረውና አሁንም የሌለው በመሆኑ ብዙውን ጊዜ ጥቂት የፖለቲካ ልሂቃን ብቻ የሚሳተፉበትና የሚወስኑበት የህይወት መስክ ሆኗል። እነዚህ የፖለቲካ ልሂቃን ደግሞ እንወክለዋለን የሚሉት የተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል ያላቸው ሲሆን በዋናነት ዘውጋዊ እና ህብረ ብሄራዊ አሰላለፍ ያላቸው ናቸው። ነገር ግን የተሻለ ለውጥ ከማምጣት እና ገዢውን ፓርቲ ከመገዳደር አንፃር ውጤታማ መሆን አልቻሉም። እንዲያውም አንዳንዶቹ ፖለቲካዊ ትግሉ ወደ አንድ እንዳይሰባሰብና እንዳይጠናከር ጋሬታ የሚሆኑበት ጊዜ አለ። ለዚህ በምክንያትነት የሚጠቀሱት ብዙ ቢሆኑም የተወሰኑት ለመጥቀስ ያህል፤

1. ከድሮም የአገራችን ፖለቲካ ለንጉሳዊያንና ለመሳፍንቱ የተተወ ጉዳይ ስለነበረ የልምድ እጥረት ወይም የፖለቲካ ተሳትፎ ውስንነት እንዲፈጠር አድርጓል።
2. በስልሳዎቹ የነበሩት ተማሪዎች አብዛኞቹ ወደ ፖለቲካው የተቀላቀሉበትና በኋላም እርስ በእርስ የተፋጁበት ሁኔታም በራሱ ለቀሪው ወይም ለተከታዩ ትውልድ በፖለቲካ የመሳተፉ ጉዳይ ከኤሌትሪክ ጋር አያይዞ እንዲያየው ስላደረገው ነው።
3. በስልሳዎቹና በኋላ የተፈጠሩት የፖለቲካ ድርጅቶችም በውስጣቸው ነፃ አስተሳሰብ የሚያራምዱትን ሁሉ በግድያና በዛቻ እንዲሰደዱ ወይም አንገታቸውን ደፍተው እንዲኖሩ ስለተደረጉ ፖለቲካው በነፃነት እንዳይጎለብትና የጥቂቶቹ ብቻ ሆኖ እንዲዘልቅ የራሱ አስተዋፅኦ ማድረጉ በዋነናት የሚጠቀስ ነው።

ለምሳሌ፡-
በህወሀት ውስጥ አንዴ አውራጃዊነት ሌላ ጊዜ የምሁር ትምክህተኝነት ሌላ ጊዜ ደግሞ ከላሲነት (አስተሳሰቡ ከለሰ ወይም በረዘ ከሚለው የተገኘ ነው) በሚሉና ማለቂያ ባልነበራቸው የስም ማጥፋት ዘመቻዎች እንዲገደሉ ወይም እንዲሰደዱ ተደርጓል። በኢህአፓም ተመሳሳይ ሁኔታ ነው የነበረው። ከዚህም ሌላ በደርግ፣ በኢህአፓ፣ በመኢሶን እና በሌሎች ኃይሎች መካካል የነበረው የእርስ በእርስ መጠፋፋት ምክንያት ብዙዎቹ በዘመኑ ወደ ፖለቲካ የተቀላቀሉ ኢትዮጵያውያን እንዲያልቁ ሆኗል። በጣም ጥቂት የሚባሉት ብቻ የአቋም ወይም የእምነት ሽግሽግ አድርገው በህይወት የመኖር እድል አግኝቷል። አንዳንዶቹ ደግሞ በአገር ቤት ፖለቲካው ማስኬድ አስቸጋሪ ሆኖባቸው በባህር ማዶ ሆነው በርቀት ፖለቲካውን የመምራት ወይም ድጋፍ የመስጠትን ሚና ይጫወታሉ። እነዚህም ቢሆኑ የራሳቸው የሆነ ውስንነት ያላቸው በመሆኑ በትግሉ ላይ ውጤት ለማምጣት አስቸጋሪ ሆኖባቸዋል። ሌላው ቀርቶ በሻዕቢያ ውስጥም ከእነ ኢሳይያስ አፈወርቅ ለየት ያለ አቋም የነበራቸው ኤርትራውያን ምሁራን “የሌሊት ወፍ” የሚል ቅፅል ስም ተሰጥቷቸው በአሰቃቂ ሁኔታ እየተለቀሙ እንዲጠፉ ተደርጓል። ሻዕቢያ ከዚያ በኋላ ነው በአቶ ኢሳይያስ ብቸኛ መዳፍ ስር የወደቀው የሚሉ አሉ።

በአገራችን ያሉት ፖለቲከኞች አብዛኞቹ በቀደምቶቹ የፖለቲካ ድርጅቶች ተሳትፎ የነበራቸው ቢሆኑም ከዚያ በፊት ከነበሩበት አሰላለፍ ተሞክሮ ወስደው የተሻለ መንገድ ይዘው እየተንቀሳቀሱ የሚገኙት በጣም ጥቂቶች ናቸው። ቀሪዎቹ ከአንዱ ወደ ሌላው ቢገላበጡም ምንም ጠብ የሚል ለውጥ ለማምጣት የተሳናቸው ሆኗል። በእርግጥ ችግሩ የአመራሩ ብቻ ላይሆን ይችላል፤ አጠቃላይ ማህበረሰባዊ የሆነ የአስተሳሰብና አመለካከት ጉዳይም ጭምር ያለው መስሎ ነው የሚታየኝ።

የፖለቲካችን መሰረታዊ ችግር በመጠፋፋት ላይ የተመሰረተ፣ ልምድና ተሞክሮ የሌለው፣ ያለን ልምድም ይሁን ተሞክሮ ደግሞ ከሌላ ዓለም(አንዴ ከምዕራብ ሌላ ጊዜ ከምስራቅ) የተኮረጀና ከእኛው አገር ነባራዊ ሁኔታ ጋር ያልተሰናሰለ(እንዲስማማ ያልተደረገ)ነው። ሌላው ችግር ደግሞ በፖለቲካ አመራሩ ዘንድ የሚታይ ነው። ይህም አብሮ የመስራት እና የመተማመን ችግር ነው። ሰጥቶ የመቀበል፣ ከራስ በላይ፣ ከፓርቲ ጥቅም በላይ፣ አገርና ህዝብ የማስቀደም ተነሳሽነት ያጥረዋል። እንዲህ ተበታትኖ እና የየራስ ፓርቲ ይዞ መታገል ነው የተመረጠው። ይህ ሁኔታ ደግሞ ለገዢው ፓርቲ የተመቸ፣ በሌላ አንፃር አማራጭና ነፃነት ለሚፈልገው ህዝብ በጣም ተስፋ አስቆራጭና አናዳጅ የሆነ መላ ቅጡ የጠፋለት ነገር ነው።

አቶ በረከት ስምኦን በመፅሐፋቸው ላይ ደጋግመው ያነሱትና እንዲታወቅላቸው የፈለጉት ቁም ነገርም የተቃዋሚዎች የእርስ በርስ ሽኩቻ ነው። ምንም እንኳ የአቶ በረከት “የሁለቱ ምርጫዎች ወግ” ከሌላው ይልቅ የራሳቸው የፀሐፊው ከንቱነት በይበልጥ የታየበት መፅሐፍ ቢሆንም አንዳንድ ስለተቃዋሚ አመራሮች ያነሷቸው ነጥቦችም እውነትነት የላቸውም ለማለት አይቻልም። እኛ በተቃዋሚነት የተሰለፍነውም ግብዝነት እስካላጠቃን ድረስ ድክመት አልነበረንም ማለት አንችልም። ዋናው ነገር “ለምን ድክመት ኖረን?” ሳይሆን መባል ያለበት ከድክመታችን የምንወጣበት ብልሀትና ጥበብ ነው ይኖረን ዘንድ ነው ግድ የሚለው። ያለመተባበራችንና ለውጥ ያለማጣታችን ጉዳይ አገራዊ ውርደት ወደ መሆን ተሸጋግሯል። ይሄ ነው በመጀመሪያ መለወጥ ያለብን። ራሳችን ለምንፈጥረው ፓርቲም “የድመት ፍቅር” ሊኖረን አይገባም። በአንድ ተሰባስቦና ተዋህዶ በአጭር ጊዜ ለውጥ የሚመጣ ከሆነ ጊዜ ሳንሰጥና ምክንያት

ሳናበዛ መሰባሰብና መዋህድ ነው ያለብን። ፓርቲ መስርቶ መኖር በራሱ የመጨረሻ ግብ ሊሆን አይገባም። ፓርቲ የሚፈጠረው ተመሳሳይ ፖለቲካዊ አመለካከት ያላቸውን ዜጎች በአንድ ለማሰባሰብና በፕሮግራሙ ላይ የሚቀመጠውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ነው። እርግጥ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በአገር ቤትም ሆነ በውጭ ያሉት ተቀዋሚዎች ጥሩ ሊባሉ የሚችሉ ጅምሮች እያሳዩ ነው፦ ለምሳሌ የአንድነት እና የብርሃን ውህደት፣ ኦህኮ እና ኦፌዴን ወደ ውህደት ለመሻጋገር መስማማት፣ የመድረክ ወደ ግንባር ማድግ፣ የመገንጠልን አይረቤነት ተገንዝበው ከፕሮግራማቸው በማስወገድ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ለመታገል እየወሰኑ ያሉት ኃይሎች፣ እነዚህ ሁሉ መሻሻሎች ስንመለከት በእውነቱ ተስፋ የሚሰጥና የሚያበረታታ ነው።

በፖለቲካችን ሌላው የሚስተዋለው ችግር በኢትዮጵያዊነት ላይ ያለው የተሳሳተና ሁለት ጫፍ የያዘ ምልከታ ነው። አንደኛው "አንድ ባህል፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ ህዝብ" በሚል መልኩ ይገለፅ የነበረው ነው። ይህ ምልከታ አንዳንዴ ከግለሰብ መብት ጋር ተጨረማምቶ የሚቀርብበት አጋጣሚም አለ። ነገር ግን የአገራችን ነባራዊ ሁኔታ የግለሰብ መብት በማስከበር ብቻ የሚያበቃ አይደለም። በእርግጥ እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት የነበራቸው ኃይሎች አንድም አማራጭ የለውጥ ኃይል የመሆናቸው ጉዳይ እየቀረ ነው ወይም አሁን ያለውን ነበራዊ ሁኔታ ተገንዝበው ሁሉን ሊያቅፍ ወደ ሚችል አቋም እየመጡ ነው የሚገኙት። ይህ በራሱ በጎ ጅምር ነው። የግለሰብ መብትም የቡድን መብትም ሳይነጣጠል ነው መከበር ያለበት።

ሌላው በዋናነት በኢህአዴግና በአጋሮቹ በኩል የሚንፀባረቀው አገሪቷን ወደ ጊዜያዊ ማህበርነት ደረጃ የሚያወርደው "ብሄር ብሄረሰባዊ" ምልከታ ነው። ይህ ምልከታ አገሪቷን በብሄር ብሄረሰቦች መልካም ፈቃድ ብቻ ህልውናዋ የተመሰረተ እንዲሆን የሚያደርግ ነው።

ይህ ዓይነቱ ፖለቲካዊ ምልከታ "የቡድን መብት ብቻ ይከበር" የሚል፣ በአገሪቷ ውስጥ ተንቀሳቅሶ መስራት ለሚፈልግ ግለሰብ ቦታ የማይሰጥ፣ የግለሰብን መብት ከግምት የማያስገባ፣ የህዝቦች አብሮ የመኖርና የማደግ ዕድል የሚዘጋ፣ ወደ መበታተን የሚወስድ አደገኛ መንገድ ነው።

በእኔ እይታ ሁለቱም የተሳሳቱ እና ጫፍ የያዙ የአገራዊነት ምልከታ ከመሆናቸውም በላይ በአገራችን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ ያላስገቡ ናቸው።

ከዚህ ይልቅ በአንድነት ላይ የተመሰረተ ብዙህነት(Diversity in Unity) ያለው ፌደራሊዝም ለእንደኛ ያለ አገር ተስማሚ የአስተዳደር ስርዓት ነው። ብዙህነት በአንድነት ሲባል ብሄሮች በኢትዮጵያዊት ጥላ ስር ለህልውናቸው እውቅና ተሰጥቷቸው፣ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር፣ በቋንቋቸው የመማር፣ የመዳኘትና የመጠቀም፣ ባህላቸውና ታሪካቸውን የመጠበቅና የማሳደግ መብት የሚያስከብር፤ እንደዚሁም ራሱን በብሄረሰብ ማቀፍ ውስጥ ማስቀመጥ ለማይፈልግ ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያዊነቱ ብቻ ራሱን የሚገፅበትና ይህን መብቱን እንዲከበርለት የሚያደርግ ነው።

ለምሳሌ ከአንድ በላይ ከሆኑ ብሄረሰቦች የሚወለዱትን ኢትዮጵያውያን በግድ ብሄራቸውን እንዲመርጡ ማድረግ ተገቢ አይደለም። እዚህ ላይ ከአሁን በፊት የሰማሁትን ከዚህ ጋር የተያያዘ አጋጣሚ ልጥቀሰው። ሰውዬው መታወቂያ ለማውጣት ወደ ቀበሌ ይሄዳል። ብሄር ተብሎ ሲጠየቅ "ብሄር የለኝም" ይላል። መታወቂያ የሚያድለው ሰው ቀና ብሎ ተመለከተውና "አማራ ነህ ማለት ነው" ብሎ ብሄር በሚለው ቦታ ላይ "አማራ" የሚል ሞልቶ ሰጠው ይባላል። እንደዚያም ሆኖ የአማራን ቁጥር አለመብዛቱ ነው የሚገርመው! ብዙህነት በአንድነት በሂደት አንድ የተጠናከረና የደረጀ ፖለቲካዊ ማህበረሰብ እንዲኖረን ከማድረጉም በአሻገር የተለያዩ ፍላጎችን የማስተናገድ ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ "ተጨቆንኩ" ከሚል ስሜት የሚነሳ ብጥብጥና ህወከት ለማስቀረት ይረዳል። መፍትሄው ከሁለቱም ጫፎችና አሁን ካለንበት ፖለቲካዊ ውዝንብር ወጥተን ወደ ተረጋጋ ፖለቲካዊ ማህበረሰብ የሚወስደን ፖለቲካዊ ትግል ነው ማድረግ ያለብን።

እንደ አገር የጋራ መግባባት ይኖረን ዘንድ በታሪካችን፣ በፖለቲካችንና በአገራችን ጉዳይ ላይ መስማማት እስከቻልንበት ድረስ በቀናነት መሄድ ያስፈልጋል። "እንዲህ ካልሆነች ወይም እንዲህ ዓይነት ቅጥያ ካልተጨመረባት አገሬ አይደለችም" የሚለው ግትር አቋም የትም የሚያደርስ አይደለም። እርግጥ ነው ይህቺ አገር የሁላችን አልነበረችም፤ አሁንም አይደለችም። ከተጠቃሚነት፣ ከእኩልነትና ከነፃነት አንፃር አገራችን የሁላችን ሆና አታውቅም። በሂደት ታግለን እስክንለውጠው ድረስ አገሪቱ የገዥዎቹና የአጋፋሪዎቻቸው ብቻ ናት። እንዲዚያም ሆኖ አገራችን በመሆኗ እንወዳታለን።

አዎ! አገራችን መውደድ ያለብን እንዳለች ከነ ችግሯ እና ከነፀጋዋ ነው። እናትህ የፈለገ ዓይነት ብትሆን በሌላ የተሻለች እናት ልትለውጣት አትችልም፤ አገርም እንደዚያ ናት። ይህ በሳይንስ ወይም በሎጂክ ቢተነተንም የማይታበል ተፈጥሯዊ ሕግ ነው። ለእኔ ኢትዮጵያ የብዙ ህዝቦች አገር መሆኗ ፀጋ ነው። እነዚህ ህዝቦች በዴሞክራሲ እና የህግ የበላይነት በሰፈነበት ፍትሀዊ ስርዓት አስተሳስሮ በፍቅር እንዲኖሩ፣ በአንድነት እንዲያድጉ ማድረግ ይቻላል። ደሞ ሁሉም ኢትዮጵያዊ አገሩን ሊወድ እንደሚችል ማሰብም ተገቢ ነው።

በመጀመሪያ ወደተነሳሁበት ነጥብ ልመለስና ፖለቲካችን ውጤት እንዲኖረው ከተፈለገ የአመራሩን ሁኔታ መፈተሽ መቻል አለበት። መሪነት ለውጥ ሳይኖረው በተወሰኑ ሰዎች ዛቢያ ብቻ የሚሽከረከር መሆን የለበትም። አንድ ፖለቲካዊ አመራር ምንም የሚታይና የሚጨበጥ ለውጥ ካላመጣ "እንዴት ነው ይሄ ነገር?" ተብሎ በአባላቱ ዘንድ የሚጠየቅና የሚገመገም ካስፈለገም ሊቀየር የሚችል መሆን አለበት። የመሪና የተከታይነት ሚና የማይቀየርና ተፈጥሯዊ የሚሆነው ለንቦች ብቻ ነው። በተለይ ከኢህአዴግ በዚሁ እንኳ

ተሸለን ብንገኝ አይከፋም። በእርግጥ በዚህም በኩል ፋና ወጊ የሆኑ ፓርቲዎች እንዳሉ አልዘነጋሁትም-ይህ ባህል በሁሉም ይኖር ዘንድ ካለኝ ፍላጎት እንጂ!

ሁሉም ነገር በወጣት ይመራ ማለትም ተገቢ አይሆንም። ልምድና ተሞክሮ በፖለቲካ ውስጥ ወሳኝነት አለው። ስለዚህ ማሰበጣጠር ነው ጥሩ የሚሆነው። ልምድ ያለውም ልምዱን ወደ ቀጣዩ አመራር ለማስተላለፍ ያስችለዋል። ልምድ ያልነበረው ደግሞ በቂ የሆኑ የፖለቲካ አመራር ልምድ እንዲኖረው የሚያስችል ዕድል ስለሚፈጥርለት የመወራረስ ሁኔታ ይፈጥራል።

በዚሁ ስለአገራችን ፖለቲካ በምንነጋገርበት ወቅት በውጭ የሚኖሩ ወገኖቻችን ሚና ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም። እነዚህ ወገኖች በተሻለ የዴሞክራሲ አገር የሚኖሩ፣ በአንፃራዊ መልኩ ጥሩ የሚባል የኢኮኖሚ አቅም ያላቸው በመሆኑ በፖለቲካው ያላቸው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም። ገዢው ፓርቲም ይህን በመገንዘብ ይመስላል በፖለቲካ ያላቸውን ተሳትፎ ለመገደብ ከአንዴም ሁለቴ ህግ እስከማውጣት ድረስ የተጓዘው(አንድ በሕገ መንግስቱ፣  ሁለት ለፓርቲዎች ባወጣው አዋጅ)።

እዚህ ላይ በጣም የሚገርመው ነገር ለራሱ ከፈረንጅም ከዓረብም ገንዘብ እየለመነ ለድል የበቃው የኢህአዴግ አመራር ከእርሱ የተሻለ የኢትዮጵያዊነት እምነት ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ዜግነት ስለቀየሩ ብቻ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ሕግ አውጥቷል። በጣም ያደጉ የሚባሉ አገሮች እንኳ ሳይቀር ጥምር ዜግነት በሚፈቅድበት ሁኔታ ኢህአዴግ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑት ያገለለበት ሁኔታ ለአገር ደህንነት አስቦ እንዳልሆነ ግልፅ ነው። በስልጣን የመቀጠል ህልሙ ወደ ቀዠት የመለወጥ አቅም ስላላቸው ነው። እንጂማ ኢትዮጵያዊ ሁሌም ኢትዮጵያዊ ለመሆኑ ቅዱሳን መፃሕፍት ሳይቀሩ የመሰከሩለት ሀቅ ነው። ነቢይ ኤርሚያስ (13፥23) **"ኢትዮጵያዊ መልኩን፣ ነብር ዥርግረጉርነቱን ይለወጥ ዘንደ ይችላልን?"** ያለው ያለምክንያት አይደለም። በጣም ጥንታዊ የሆነ ማንነትና ባህል ያለን ህዝቦች መሆናችንን ለመገለፅ ነው።

በውጪ የሚኖሩ ወገኖቻችን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ያላቸው ሚናና ተፅዕኖ ቀላል እንዳልሆነ ከላይ ገልጫለሁ። ስለዚህ ያላቸውን ልዩነቶች በማጥበብ የተባበረ ኃይል ወደ መሆን ደረጃ መሸጋገር፣ የሚያደርጉት ድጋፍ ደግሞ በመርህ ላይ የተመሰረተ፣ የሚታይና የሚዳሰስ ለውጥ የሚያመጣ እንዲሆን ማድረግ፤ ተስፋ ሳይቆርጡና ሳይሰለቹ ጠንክረው መስራትና መንቀሳቀስ አለባቸው። በዋናነት ደግሞ ትግሉ እንዴት ነው መካሄድ ያለበት በሚለው ጉዳይ ላይ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋል።

በመጨረሻ የምለው ነገር ቢኖር አሁን በአገራችን ያለው አስቸጋሪ የፖለቲካ ሁኔታ በትግል ሊለወጥ የሚችል ነው። የምንለውጠው ደግሞ እኛ ዜጎቹ ብቻ ነን። በዚህ እምናለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

(በፍትሕ ጋዜጣ የጥር 4/2004 ዓ/ም እትም ላይ የወጣ)